የጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ዘርፍ

ሀገር አቀፍ የትምህርት ብርሃን ምዘና ማስፈጸሚያ ማኑዋል

ጥር/2013

መግቢያ

በመደበኛው ወይንም በመሰረት ትምህርት ተሳትፎ ያልነበራቸው በርካታ ጎልማሶች ቢኖሩም በራሳቸው ጥረት ወይም በታይማኖት ትምህርቶች ታግዘው ማንበብ እና መጻፍ እንዲሁም ማስላት ቢችሉም እንደ መሀይም በመቆጠራቸው የመሰረታዊ ትምህርትን መረጃ ያዛባል

ይህም

- አማካኝ የትምህርት ዕድሜ(Average year of schooling)
- የተማሩ ሰዎች ቁት (National Literacy Account) የተዛባ ይሆናል።

መግቢያ

ከ1945 እ.አ.አ ጀምሮ ዩኔስኮ የመሰረተ ትምህርት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ያስገደዱት ሁለት አበይት ምክንያቶች ናቸው።

እነሱም

- “ማይምነት (ማንበብና መፃፍ አለመቻል) ለልማት ዋንኛው መሰናክል መሆኑ

እና

- “መሰረተ ትምህርት (ማንበብና መፃፍ መማር) ሰብአዊ መብት መሆኑ ናቸው

መሰረታዊ ትምህርት በኢትዮጵያ

- በኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት መስጠት የተጀመረው በኃይማኖት ተቋማት ውስጥ ነው። የአብነት እና መድራሳ ትምህርት
- በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሚሽነሪዎች መሰረተ ትምህርትን ለማስፋፋት ሞክረዋል
- ዳግማዊ ሚኒሊክ በ1889 እንዲሁም ንግስት ዘውዲቱ በ1921 ዓ.ም መሰረታዊ ትምህርትን ለማስፋፋት መመሪያ አውጥተው ነበር
- አጼ ሚኒለክ የኃይማኖት ተቋማት ማንበብ እና መጻፍ እንዲያስተምሩ መመሪያ አውጥተዋል።

ይቀጥላል

በ1936 ዓ.ም ሁሉም ይማር መርህ በሁለት ዓላማዎች ላይ ተመስርቶ ወጣ

- ማይምነትን ማስወገድ (Eradication of Literacy)

እና

- ንጽህና አጠባበቅን ማሻሻል(Improving Hygiene)

ለነዚህም ሁለት መምህራንን የሚያሰለጥኑ ተቋማት ተመስርተዋል።

በ1954 ዓ.ም ብሔራዊ የፊደል ሰራዊት በሚል የበጎ ፍቃደኞች ትምህርት ለመስጠት ተሞክሯል

ይቀጥላል

- በ1959 ዓ.ም በመንግስት ደረጃ በትምህርት ሚኒስቴር የመጀመሪያው የጎልማሶች ትምህርትን የሚመራ **“የጐልማሶችና ማይማን ትምህርት ዋና ዳይሬክሲዩን”** ለብቻው ተቋቋመ

ይቀጥላል

- በደርግ ዘመነ መንግሥት መሠረተ ትምህርት እድገት በጎበረት የእውቀትና የስራ ዘመቻ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የታየበትና በአራት ቋንቋዎች ይሰጥ የነበር ነው።
- በ1971 ዓ.ም መጨረሻ አገር አቀፍ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ (National literacy campaign) ለኢኮኖሚና ባህል እድገት በሚል ትኩረት ተደረጎ ተጀመረ። ይህ ፕሮግራም እሰከ 1982 ዓ.ም በ15 የብሄረሰብ ቋንቋዎች ይሰጥ ነበር በዚህም በርካታ ጎልማሶች ከማይምነት ነጻ ወጥተዋል ፣ በርካቶችም ወደ መደበኛ ትምህርት ገብተው ትምህርታቸውን መቀጠል ችለዋል

ይቀጥላል

- ከደርግ በኋላም M¨iኛ ያልሆነ ፤ ተግባራዊ የጎልማሶች ት/ት (FAL) ተብሎ ሲሰጥ ነበር
- በተለይ በአራተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም መንግሥት ለጎልማሶች ትምህርት የተሻለ ትኩረት ተሰጥቶት የተ.ተ.ተ.ን.ት (IFAE) በመባል በቅንጅት እንዲሰጥ አቅጠጫ ነበረው
- በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድና በአምስተኛው የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሃ ግብር የበለጠ ትኩረት ተሰጥቶት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት በቅንጅት እንዲሰጥ ጥረት ሲደረግ ቆይቶአል

ይቀጥላል

ነገር ግን በርካታ ጎልማሶች ተገቢውን ምዘና ባለማግኘታቸው ቀጣይ በሆነ የትምህርት እና ስልጠና እድል ተጠቃሚ ሳይሆኑ ቀርተዋል።

ይህም የሀገራችንን የአገራችንን አማካኝ የትምህርት ዕድሜ አነስተኛ አድርጎታል።

በልዩ ልዩ መንገድ ማንበብ መጻፍና ማስላት የሚችሉ ሰዎች በአግባቡ ተመዝነው ወደ ተማሩ ዜጎች መረጃ ቋት ባለመካተታቸው ሀገራችን ዝቅተኛ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮቸረ ጋር ስትነጻጸር መሰረታዊ ትምህርት ያገኙ ዜጎች ቁጥር ዝቅተኛ ነው

ሀገር አቀፍ የትምህርት ብርሃን ምዘና መርሃ ግብር መነሻ ጽንሰ ሀሳቦች

- የጎልማሶች ህይወትና የስራ መስኮች መልከ ብዙ እንደመሆናቸው ጎልማሶች በመደበኛ እና በኢመደበኛ የሚጠቀሙባቸው የመሰረት ትምህርት ዓይነቶች ብዝሃነት እንዳላቸው የነበረው ግንዛቤ አነስተኛ መሆን
- የመሰረታዊ ትምህርት ሰዎች ሃሳባቸውን ለሌሎች ለማስተላለፍ የሚጠቀሙባቸው የተግባቦት መንገዶች ፈርጀ ብዙ ከመሆናቸው ባሻገር የመሰረታዊ ትምህርት አካላት መሆናቸውን ያለመገንዘብ እና ትኩረት ያለመስጠት

- በተለምዶ የምንጠቀምባቸው የመሃይማንና ከመሃይምነት የተላቀቁ ሰዎች ሃሳባዊ ድንበሮች ከተጨባጭ የራቁ በመሆናቸው ማህይም የምንላቸው ጎልማሶች ሲያነቡ ፣ሲጽፉ እና ሲያሰሉ መታየታቸው የተለመደ መሆኑ
- የትምህርት ብርሃን ምዘናን በሁሉም መህገሪቱ ክልሎች በመተግበር የወታቶችንና የጎልማሶችን መልከ ብዙ የማንበብ ፣የመጻፍና የማስላት ክህሎት በመለየትና በሚያገኑት ውጤት መሰረት እውቅና መስተት እና ወደሚቀጥለው ትምህርትና ስልጠና ዕደል ተጠቃሚነት ማሸጋገር

ሀገር አቀፍ የትምህርት ብርሃን ምዘና ዓለማ

- **በተለያዩ መንገድ የማንበብ መጻፍና ማስላት፡-** የወጣቶችንና ጎልማሶችን የማንበብ፣የመጻፍና የማስላት ክህሎት በመመዘን በሚያገኙት ውጤት መሰረት ዕውቅና መስጠት፣
- የጎልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ፕሮግራሞች ጥራትና ተገቢነት ለማስጠበቅ እንዲሁም ቀጣይነቱን ማረጋገጥ
- የተማሩ ሰዎች ቋት (National Literacy Account) ማሳደግ

ይቀጥላል

ሰዎች ከትምህርት ቤቶች ወይም ከመማሪያ ተቋማት ውጪ በተለያዩ መንገዶች የቀሰሙዋቸውን የማንበብ፣ የመጻፍ፣ የስሌትና የሕይወት ክህሎት እውቀቶች እውቅና የሚሰጥና ለበለጠ የሕይወት ዘመን ትምህርት /life long learnig/ ያላቸውን ተደራሽነት ለማስፋት

እነማን ይመዘናሉ?

- በተለያዩ መንገዶች የማንበብ፣ መጻፍና ማስላት ክህሎት ያዳበሩ (ለምሳሌ ፦ በአብነት፣ በመድረሳ ትምህርት እና በሌሎች መንገዶች የተሳተፉ) ወጣቶችና ጎልማሶች
- በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሀ-ግብር የተሳተፉ ወጣቶችና ጎልማሶች

ይቀጥላል

ምዘናው የሚያካትታቸው ይዘቶች

የምዘናው ይዘት የሚመሰረተው ለጎልማሶች መሰረታዊ ትምህርት መርሀ-ግብር የተቀመጠውን አጥጋቢ የመማር ብቃት መለኪያ (MLC) መሰረት አድርጎ

- የማንበብና መጻፍ ክህሎት
- መሰረታዊ የሂሳብ ስሌቶች ክህሎት
- የክህሎት ልማት(የግልና የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ)

ይቀጥላል

የምዘናው ዓይነት

ምዘናው በዋናነት በወረቀትና በእርሳስ የሚከናወን የፊተና አጻጻፍ ዕነትና ዘዴዎችን የተከተለ ይሆናል።

ምዘናው የሚሰጥበት ቋንቋ

ምዘናው በሚካሄድባቸው በሁሉም ጣቢያዎች የተመዘኙ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ወይም በአካባቢው በሚነገር ቋንቋ የሚዘጋጅና የሚሰጥ ይሆናል

ምዘናው የሚካሄድባቸው ቦታ

የጎልማሶች ትምህርት መስጫ ጣቢያዎች የሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ፤የገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከላትና ጤና ኬላዎች ሲሆኑ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የወረዳው ትምህርት ጽ/ቤት ከህብረተሰቡ ጋር በመነጋገር የሚወሰን ይሆናል።

ምዘናው የሚሠጥበት ጊዜ

ምዘናው የሚሰጥበትን ጊዜ በሚመለከት የተመዘኞቹን ፍላጎት መሰረት በማድረግ የአካባቢው የወረዳ ት/ጽ/ቤት በሚያወጣው መርሀ- ግብር መሰረት በዓመት ሁለት ጊዜ ወጥነት ባለው መልኩ በሁሉም ምዘና መስጫ ጣቢያዎች የሚከናወን ይሆናል።

ይቀጥላል

የምዘናው ውጤት አሰጣጥ

- ማንበብ ከ30%
- መጻፍ ከ25%
- ማስላት ከ30%
- የልማት ክህሎት ከ15%

- **የምስክር ወረቀት አሰጣጥ፡-**

- የምስክር ወረቀት በመደበኛው ትምህርት ያለውን አቻ የክፍል ደረጃ መሳተፍ የሚያስችል መሆኑን የሚገልጽ ይሆናል።
- የምስክር ወረቀቱ ህጋዊ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው በትምህርት ቤቱ ር/መምህር የተፈረመና የተቋሙ ማህተም ያረፈበት ይሆናል

- **የሽግግር ሂደት፡-**
  - ምዘናውን ተመዘነው 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ያላቸውና የምስክር ወረቀት ያገኙ ተመዛኝ ወጣቶችና ጎልማሶች በመደበኛው ትምህርት ፕሮግራም 3ኛ ክፍል ካጠናቀቁት ጋር አቻ ይሆናሉ
  - እንደ ፍላጎታቸውም የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠና ወይም ወደ ሚቀጥለው የክፍል ደረጃ ገብተው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ።

የባለድርሻ አካላት

- የፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር
- የክልል/ከተማ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ
- የዞን/ ክፍለ ከተማ ትምህርት መምሪያ
- የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት
- የቀበሌ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ
- የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር
- በመማመሪያ ጣቢያ ደረጃ አስተባበሪ
- አመቻቾች

የክልል ትምህርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

- ለሚመለከታቸው በሙሉ ስለ ትምህርት ብርሃን ምዘና ግንዛቤ ይፈጥራል
- በማዕከል የተዘጋጀውን የምዘና ጥያቄ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ያስተረጉማል
- ምዘናው በተያዘለት ጊዜ መካሄዱን ይከታተላል
- የተመዘኑ ተሳታፊዎችን መረጃ ይሰበስባል ይተነትናል ወደሚመለከተው የበላይ አካል ያስተላልፋል
- የምስክር ወረቀት አሰጣጡን ይከታተላል ድጋፍ ያደርጋል
- ሽግግሩ በወጥነት ስለመተግበሩ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል
- ናሙና የምስክር ወረቀት ያዘጋጃል
- አጥጋቢ ውጤት ያላመጡ ጎልማሶች በዳግም ምዘና እንዲሳተፉ ያደርጋል

የክፍለ ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- ለሚመለከታቸው በሙሉ ስለ ትምህርት ብርሃን ምዘና ግንዛቤ ይፈጥራል
- በማዕከል የተዘጋጀውን የምዘና ጥያቄ ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋዎች ያስተረጉማል
- ምዘናው በተያዘለት ጊዜ መካሄዱን ይከታተላል
- የተመዘኑ ተሳታፊዎችን መረጃ ይሰበስባል ይተነትናል ወደሚመለከተው የበላይ አካል ያስተላልፋል
- የምስክር ወረቀት አሰጣጡን ይከታተላል ድጋፍ ያደርጋል
- ሽግግሩ በወጥነት ስለመተግበሩ የሙያ ድጋፍ ያደርጋል
- ናሙና የምስክር ወረቀት ያዘጋጃል
- አጥጋቢ ውጤት ያላመጡ ጎልማሶች በዳግም ምዘና እንዲሳተፉ ያደርጋል

የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

- በወረዳው ለሚገኙ ትምህርትና ስልጠና ቦርድ ለመዛኝ መምህራንና አመቻቾች እና ለሚመለከታቸው በሙሉ ስለ ትምህርት ብርሃን ምዘና ግንዛቤ ይፈጥራል
- ጎልማሶች እና ወጣቶች ለምዘና እንዲመጡ እና እንዲመዘገቡ አቅጣጫ ይሰጣል
- ተመዛኞች ምዘናውን ከመውሰዳቸው በፊት ለ5 ቀን ስለ ምዘናው ዓይነትና ይዘት ቅድመ ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል
- ምዘናው በተያዘለት ጊዜ መካሄዱን ይከታተላል
- የተመዘኑ ተሳታፊዎች መረጃን ይሰበስባል፤ይተነትናል ለሚመለከተው የበላይ አካል ያስተላልፋል
- የምስክር ውረቀት ለትምህርት ቤቶች እንዲደርስ ያደርጋል
- አጥጋቢ ውጤት ያላመጡ ጎልማሶች በዳግም ምዘና እንዲሳተፉ ያደርጋል

የትምህርት ቤት ር/መምህር ተግባርና ኃላፊነት

- ለምዘና የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ያሟላል
- ተመዛኞች ምዘናውን ከመውሰዳቸው በፊት ለ5 ቀን ስለ ምዘናው ዓይነትና ይዘት ቅድመ ግንዛቤ እንዲፈጠርላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል
- ከአስተባባሪው ጋር በመሆን የተዘጋጀውን ፈተና ለተመዛኞች እንዲደርስ ያስተባብራል
- የምስክር ወረቀት ያዘጋጃል
- ምዘናውን ያስተባብራል
- የምስክር ወረቀት አሰጣጡን በበላይነት ይከታተላል ይቆጣጠራል
- መዛኞች ስለመመደባቸው ክትትል ያደርጋል
- አጥጋቢ ውጤት ያላመጡ ጎልማሶች በዳግም ምዘና እንዲሳተፉ ድጋፍ ያደርጋል

የአመቻቾች ተግባርና ኃላፊነት

- የምዘና ክፍሎች ለምዘና ምቹ የማድረግ ስራ ይሰራሉ
- ለምዘና ለሚመጡ ጎልማሶች ገለጻ ያደርጋሉ
- ተመዛኞች ምዘናውን ከመውሰዳቸው በፊት ለ5 ቀን ስለ ምዘናው ዓይነትና ይዘት ቅድመ ግንዛቤ ይፈጥራሉ
- ለምዘና የሚመጡ ተመዛኞችን ምዝገባ ያደርጋሉ
- በጣቢያው የተመዘኑትን ተመዛኞች አጠቃላይ መረጃ ይይዛሉ
- ምዘና ይሰጣሉ
- ፈተና ያርማሉ የምዘና ውጤት መረጃ ያደራጃሉ
- አጠቃላይ ሪፖርት ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ
- አጥጋቢ ውጤት ያላመጡ ጎልማሶች በዳግም ምዘና እንዲሳተፉ ድጋፍ ያደርጋል

የተመዛኞች ተግባርና ኃላፊነት

- በጎልማሶች ትምህርትና በተለያየ መንገድ ማንበብ፣ መጻፍና ማስላት ተሚችሉ መሆናቸውን አምነው በፍላጎታቸው ለመመዘን ይመዘገባሉ
- ምዘናውን ከመውሰዳቸው በፊት ለ5 ቀን ያህል ስለምዘናው ዓይነትና ነነዘት በምዘና ጣቢያ ቀርበው ቅድመ ግንዛቤ ይወስዳሉ
- በፈተና ቀን ሰዓቱን አክብረው በመገኘት ምዘናቸውን ይወስዳሉ
- በምዘናው አጥጋቢ ውጤት ያላመጡ ከሆነ ለዳግም ምዘና ራሳቸውን ያዘጋጃሉ

የክትትልና ድጋፍ ስርዓት

የትምህርት ብርሃን ምዘና ተግባራዊ ለማድረግ በትምህርት ሴክተሩ በየደረጃው ባለው መዋቅር ቅድመ ምዘና ምዘና እና ድህረ ምዘና ጊዜ አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ተጠናክሮ ይደረጋል፣በአፈጻጸሙ ላይ ግምገማ ይደረጋል በየደረጃውም ግብረ መልስ ይሰጣል።

አመሰግናለሁ